በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# ባልንጀራዬ ማነው?

## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com

***ቦታ፡-*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

ጥቅምት ፩ ቀን ፳፻፬ ዓ.ም.

# <u>ባልንጀራዬ ማነው?</u>

- ይህ ጥያቄ አንድ የሕግ አዋቂ ጌታችንን ሊፈትነው ወዶ የጠየቀው ነው፡፡ ጌታችንም በደጉ ሳምራዊ ምሳሌ ምላሽ ሰጥቶታል፡፡ *<u>ሉቃስ 10፡25-37፡፡</u>*

1. *ኦርቶዶክሳዊው ክርስቲያን ማነው?*

- የኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያን አስተሳሰብ ከዓለማዊ ወይም ከተራው ሰው የተለመደ አስተሳሰብ ይለያል፡፡
- ኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያኖች የምንባለው በምናሳየው የመታወቂያ ካርዳችን አይደለም፡፡
- በዓላትን እያከበርን፣ ታቦታትን እያነገስን ከቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እየተሳተፍንም ጥልቅ ሕይወት አጥተን ኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያን ሳይሆኑ መገኘት አለ፡፡
- ይህም ወንበዴዎች ለደበደቡት ሰው ሌዋዊው (ዲያቆን) ትኩረት ሳይሰጥ ባለፈበት ሁኔታ ውስጥ ተገልጿል፡፡
- በውጪ ኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያኖች መስለን ብንታይ እግዚአብሔር በዚህ ደስ አይሰኝም፡፡ ይልቁኑ በውስጡ ሰውነታችን ስለሚያስፈልገን ነገር ይጠይቀናል እንጂ!
- ቅዱስ አውግስጢኖስ ‹‹ወንድሞቼ ሆይ ደስ ይበላችሁ! ይልቁኑ በመንፈስቅዱስ ስጦታ ታተማችሁ እንጂ ክርስቲያኖች ብቻ የሆናችሁ አይደላችሁም›› በማለት አሳምኖ ላጠመቃቸው እንደተናገረው ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ሕይወታቸው በመሠረታዊነት በክርስቶስ ፈቃድ የሚመራ እንጂ ጽንፈኞች ወይም ትዕግሥት አልባ አለመሆናቸውን ተናግሯል፡፡

# ባልንጀራዬ ማነው?

- ክርስቶስ በውስጣችን፣ በልቦናችን፣ በሐሳባችን፣ በስሜታችን እንዲሁም በሁለመናችን በመኖሩ በእውነት እርሱን በመምሰላችንና የጽንፈኛ ቡድን ወይም ዘር አባሎች በመሆን መካከል ከፍተኛ ልዩነት ይታያል፡፡
- ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹*ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ፡፡*›› ***ፊል 4፡13***፣ <<ክርስቶስም በልባችሁ በእምነት እንዲኖር›› ***ኤፌ 3፡16-17*** በማለት የነገረንም ይህንኑ ነው፡፡
- ክርስቲያኖች ክርስትናን ሐሳብ፣ የሐሳቦች ስብስብ ወይም የጽንፈኞች ክንፍ አድርጎ አይመለከቱትም፡፡ ሁሉም የአሁኑን ጊዜ የሚመለከቱ ናቸውና፡፡
- ኦርቶዶክሳዊ ክርስትና በክርስቶስ የሆነ እርሱም እያንዳንዳችን የምንኖረው እውነተኛ ሕይወት ነው፡፡
- ‹‹*ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ፡፡*›› ***ዮሐ 6፡56*** የሚለው የምስጢረ ቁርባን ኃይለ ቃል የሚያረጋግጥልንም ይህንኑ ነው፡፡
- ኦርቶዶክሳዊውን የተዋሕዶ ክርስትና ከሌለች ማኅበራዊ ወይም የተሐድሶ አመለካከቶች/አስተሳሰቦች የሚለየውም ይኸው ነው፡፡
- በታሪክ ሁሉም የተሐድሶ አስተሳሰብ መሪዎች  በጣም አስደናቂ አስተሳሰቦችን አመንጭተዋል፣ በተግባር ላይ ለማዋልም ሆነ በሌሎችም ላይ ተጽእኖ ለማሳደር ታላቅ ተጋድሎ አድርገዋል፡፡ በመጨረሻ ግን እነርሱም አስተሳሰቦቻቸውና አመለካከቶቻቸውም አብረዋቸው ሞተዋል፡፡

# ባልንጀራዬ ማነው?

- ጌታችን ውብ የሆነውን መመሪያ ሲሰጠን መጥቶ በእኛ ላይ አደረ እኛም በሕይወት እንኖር ዘንድ ሕይወት ሰጠን እንጂ መመሪያዎቹን እንድንተገብራቸው ብቻ የሰጠን አይደለም፡፡
- በአማንያኑ ውስጥ መኖር የሚችል ብቸኛው መሪ እርሱ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው፡፡
- ኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያን ማለት ይህ ነው፡፡
- ኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያን ማለት የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ፣ የእግዚአብሔር የእጁ ሥራ የሆነ ፍጡር ማለት ነው፡፡ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር በመስማማት እውነተኛ ክርስቲያን የሚሆነው በዚሁ መንገድ ነው፡፡

*2. ሕይወቱን በሥራ የሚገልጠው ኦርቶዶክሳዊው ክርስቲያን ማነው?*

- ክርስቲያኖች ዘወትር እንደሚጠቀሙበትና እንደሚያስፈልጋቸው አየር በተግባር የሚገለጥ ሕይወት እስኪገኝባቸው ድረስ በትጋት መጸለይ ያስፈልጋቸዋል፤ ክርስቲያን ያለ እግዚአብሔር ሊኖር አይችልምና፡፡
- ጥቂት ጊዜ መጸለይ ከእግዚአብሔር ጋር ለመኖር ወይም እግዚአብሔር በመካከላችን እንዲገኝ በቂ እንደሆነ አድርጎ ማሰብ ተገቢ አይደለም፡፡ ይልቁኑ ጸሎት ከእግዚአብሔር መለኮታዊ ሕይወትን ተቀብለን መንፈሳዊ አየርን የምንተነፍስበት ዕድል ነው፡፡
- ጸሎት ሕይወታችን ለእግዚአብሔር የተከፈተ እንዲሆን እግዚአብሔርም ወደ ሕይወታችን እንዲገባ የሚያደርግ ነው፡፡ በጸሎትም ከመለኮት ሕይወት የታደልን እንሆናለን፡፡

# <u>ባልንጀራዬ ማነው?</u>

*2. ሕይወቱን በሥራ የሚገልጠው ኦርቶዶክሳዊው ክርስቲያን ማነው?*

- ሸክላ ሠሪ ከአፈር ለሚያበጀው ዕቃ መልካም ቅርጽን እንደሚፈጥርለት እግዚአብሔርም በጸሎት አማካይነት ይቀርጸናል፡፡
- ዓለማችን፣ ክርስትናችን፣ እንዲሁም ቤተ ክርስቲያናችንም የበዛ ጸሎት እንደሚያስፈልጋት እናምናለን፤ ጸሎት መረጋጋትን የምናገኝበት ፈጽሞም የምንለወጥበት መሣሪያ ነውና፡፡
- ጌታችን በታቦር ተራራ ሲጸልይ ሳለ በፊታቸውም ተለወጠ፥ ፊቱም እንደ ፀሐይ በራ፥ ልብሱም እንደ ብርሃን ነጭ ሆነ፡፡ እኛም በደሙ ስንታጠብ እንዴት እንደሚያነጻን አስተማረን፡፡ *<u>ማቴ 17</u>*
- ስለዚህ በማለዳና በምሽት፣ በጎዳና፣ በሥራ ገበታ፣ በትምህርት ቤት፣ በመኝታ ክፍላችን፣ ዕረፍት በምንደርግበትም ጊዜ ሳይቀር መለኮታዊውን እስትንፋስ ጸሎትን እንደምንተነፍስ ለእግዚአብሔር ቃል እንግባ፡፡
- እኛና እግዚአብሔርን ያስተሳሰረ ምስጢራዊ የሆነ ልዩ ውሳጣዊ ሕይወት ለመምራት ያበቃን ኃይለ እግዚአብሔር እንዳለ ልንገነዘብ ይገባናል፡፡
- በማኅፀን ያለ ፅንስ በእናቱ ደም ሥር በኩል ሁሉን እንደሚያገኝ የክርስቲያንም ጸሎት መለኮታዊ በረከትን በመቀበል እውነተኛ ሕይወትን ሁሉን በሚሞላ በክርስቶስ የምንቀዳጅበት ሥር ነው፡፡
- እንዲሁ ሁሉ ቃሉ የመለወጥ ኃይል አለውና ክርስቲያኖች ቃለ እግዚአብሔርን ማንበብ ሊያዘወትሩ ይገባቸዋል፡፡

# ባልንጀራዬ ማነው?

*2. ሕይወቱን በሥራ የሚገልጠው ኦርቶዶክሳዊው ክርስቲያን ማነው?*

- ጌታችን ደቀ መዛሙርቱን ‹‹እናንተ ስለ ነገርኋችሁ ቃል አሁን ንጹሐን ናችሁ፡፡›› *ዮሐ 15፡2* እንዳላቸው ቃለ እግዚአብሐየር ያነጻል፡፡
- አባ እንጦንስ የጌታችንን ጥሪ ተቀብሎ ብዙዎችን ወደ መንፈሳዊነት የመራ አባት ነው፡፡ ዛሬም ቢሆን ብዙዎች ስለርሱ ሕይወት ሲሰሙ ይማረኩበታል፡፡
- ስለዚህ ክርስቲያኖች ሆይ! ቃለ እግዚአብሔር ክርስቲያናዊ ሕይወትን እንድንመራና ክርስቲያናዊ አስተሳሰብ እንዲሰለጥንብን የሚያደርግ መሆኑን እንወቅ፡፡
- ቅዱስ ቁርባንን መቀበልም ከክርስቶስ ጋር ብቻ ሳይሆን ከእኛ ጋር ከምስጢረ ቁርባን ከሚሳተፉ ወንድሞቻችንንና እህቶቻችን ጋር እንድንዋሐድ የሚያደርገን ነው፤ ሁሉም ከአንዱ ሥጋ ይበላሉ ከአንዱ ጽዋ ይጠጣሉና፡፡
- ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ወደ ቅዱስ ቁርባን ሲቀርቡ ዓለሙን ሁሉ የሚወደውን ክርስቶስን ይቀርቡታል፡፡ ‹‹እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና፡፡›› *ዮሐ 3፡16፡፡*
- ከቅዱስ ቁርባን ስንሳተፍ ከራሳችንም ሆነ ከዓለሙም ጋር ሰላም እንሆናለን፡፡
- ኦርቶዶክሳውያን በቅዳሴው ከሰማያውያን መላዕክት፣ ከቅዱሳኑና አብረውንም ከሚያስቀድሱት ጋር አንዱም ሳይቀር በአንድነት ሆነን ወደ እግዚአብሔር እንቀርባለን፣ ልቦናችንንም ለርሱ እንከፍታለን፡፡ በቅዳሴውም ክርስቶስ እግዚአብሔር በሕይወታችን የመላ ይሆናል፡፡

# ባልንጀራዬ ማነው?

*2. ሕይወቱን በሥራ የሚገልጠው ኦርቶዶክሳዊው ክርስቲያን ማነው?*

- አሥራ ሁለት ዓመት ደም ሲፈሳት እንደኖረችው ሴት ጌታችንን መንካት ቢሳነንም የርሱ በሆኑት በቆሰሉትና በሚማቅቁት አካላቶቹ አማካይነት ልንነካው እንችላለን፡፡
- ዛሬ አካላቸው በመጉደሉ የተነሳ፣ በሕመም፣ በእርጅና ወይም ምክንያት በማይቀርብለት ሐዘን  የተነሳ በአልጋ የወደቁ ብዙዎች ናቸው፡፡
- እንደ ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ከቆሰሉ በእርግጥም የክርስቶስ ከሆኑት ጋር ስንሆን ልንገኝ ይገባል እንጂ አቁሳዮች፣ አሲድ በሌላው ሰውነት የምንደፋ፣ በስለት የምናጠቃ፣ የሰውን ስም የምናጠፋ… ልንሆን አይገባንም፡፡ <u>ማቴ 25፡35-</u>… የሚለን በዚህ ነውና፡፡

*3. ኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያን ለባልንጀራው እስከምን ይደርሳል ባልንጀራውስ ማነው?*

- ከክርስቶስ እግዚአብሔር ጋር የሆነውን ኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያን ባልንጀራው ማን እንደሆነ ብንጠይቀው ሁሉን በክርስቶስ ልብ የሚወድ መሆኑን ይነግረናል፡፡ አምላካችን ክርስቶስ የሚጠላው እንዳለው ብንጠይቀው መልሱ ምን እንደሆነ አናውቅም? እርሱ ጥላቻን አያውቅም ዓለሙን ሁሉ ይወዳልና፡፡
- እርሱ አምላካችን ክርስቶስ የሰቀሉትን ጠላቶቹን ሳይቀር ይወዳል፡፡ እርሱ ትክክለኛው ጠላት ያ ሰው ወይም ሌሎቹ ሳይሆኑ የቀደመውን የሰው ልጅ ተፈጥሮ ያሳደፈው እንዲሁም የዚህ ምንጭ የሆነው ሰይጣን እንደሆኑ ያውቃል፡፡
- ሌላውን ሰው ለእኛ እንግዳ ወይም ባዕድ የሚያደርገውም ይኸው ነው፡፡ እኛ ክፉ ሐሳብና ኃጢአት የወደቀ ሰው በሌላ ጠላት መያዙን ስለምናውቅ እንደ እንግዳ ወይም እንደ ባዕድ አንቆጥረውም፡፡ ያውም የያዘው ያሰረው የሁላችን ጠላት ሰይጣን ነው፡፡

# ባልንጀራዬ ማነው?

### *3. ኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያን ለባልንጀራው እስከምን ይደርሳል ባልንጀራውስ ማነው?*

- በቀዳሜ ሰማዕት ቅዱስ እስጢፋኖስ ሕይወት የተገለጠልንም ይኸው ነው፡፡ ***<u>የሐዋ 7፡1-…</u>***
- ሰው ወደ እግዚአብሔር በቀረበ ቁጥር ልቡ ያድግና ፍቅርን ይሞላል፤ ሰውን ሁሉ ይወዳል፤ በሕይወቱ በሚገኝ ሁሉን ማድረግ በሚቻለው በክርስቶስ ልብ ይወዳልና፡፡ ጠላት አድርገን የምንቆጥርበት ምንም ምክንያት ቢኖረን ሁሉን ትተን ወንድማችን እንደሆነ እንቀበለዋለን፡፡
- ኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያን የሚመራው በክርስቲያናዊ ሕይወት ነው፤ በክርስቶስ ልብ ይወዳል፣ ያስባልና፡፡
- ማንኛውንም ሐሳብ፣ አመለካከት፣ … ወዘተ ከመቃወሙ በፊት የሀሳቦቹን በጎ ጎናቸውን ይመለከታል፡፡
- ስለማኅበራዊ ፍትሕና ስለሌሎችም በሰብአዊነት እንዲሠራ የሚያስችሉትን ይመረምራል፤ በተከፈተ አእምሮ አጥንቶ የሚቀበለውን ይቀበላል የሚነቀፈውንም ገንቢ በሆነ መልክ ይነቅፈዋል፡፡
- ሰዎች አንድን ነገር አሟልተው ለማቅረብ ያልቻሉበት እጥረት ቢገኝባቸውም በውስጣቸው የሚገኘውን ውበት ባልሻገተና ባልተበላሸ ከማንኛውም ክፉ ነገር በፀዳ አእምሮ ይመለከታል፡፡
- ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹እንዲያስተምረው የጌታን ልብ ማን አውቆት ነው? እኛ ግን የክርስቶስ ልብ አለን፡፡›› ***<u>ኣል ቆሮ 2፡16፡፡</u>*** ኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያን ልዩ የሆነ ተወዳጅ አስተሳሰቦች ያሉት፤ ልዩ በሆነው በክርስቶስ ልብም የሚያስብ ነው፡፡
- የክርስቲያን ሕይወቱ ፍቅርን በሚያድል፣ ፍቅርን በሚያበቅል፣ ፍቅርን በየትኛውም የዓለም ክፍል በሚያስፋፋ በክርስቶስ የተቀረጸ ነው፡፡
- ክርስቲያን ይልቁኑ በአምላካችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅርና በርሱም ባለው በጸና እምነቱ እንጂ አንዳችንም ነገር ከራሱ ወይም ከሥጋ ችሎታው አፍልቆ አይሠራም፡፡ በዚህ የተነሳ በሕዝቡ መካከል ራሱን በትሕትና የሚገልጥ ሆኖ ታላላቅ ነገሮችን መቀዳጀት ይቻለዋል፡፡ አምላካችን በዚህ ሕይወት ያኑረን!

# ወስብሐት ለእግዚአብሔር፡፡

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org